# ያበጠው ይፈንዳ

ሀገሬን ለማዳን ቀኑ ቢርቀኝም

ፈተናው በርክቶ ጭንቀት ቢከበኝም

አንገቴን ደፍቼ ማልቀሴ አልቀናኝም

ለቅሶዬ የፍቅር ቢሆን... አይገርመኝም

የልቤ ቋጠሮ...አልተፈታልኝም፤

ውስጤ ቅጥል ብሎ ደህና ቢመስለኝም

ልቤ ግን ተጽናንቶ ቀና-በል ቢለኝም

ቀን ይቆጥር ይዞአል... ግን አልነገረኝም።

የልቤን ማን አውቆ ኃቁን ይንገረኝ

ፍቅር አስጨንቆኝ ፍራኃት ተናንቆኝ

ቀን ይፍታው ማለቴ ፍርኃት መስሎብኝ

ትግስት እንደ ፍርኃት ለምንስ ታየብኝ፤

ወኔዬ ገንፍሎ እንዲህ እየናጠኝ

በደሉ በዝቶብኝ ግፉም አንገሸግሾኝ

በገዛ አገሬ ተሰድቦ፣ተንቆ፣ሕይወት ሰቀጠጠኝ

ተዋርዶ ከመኖር ሞቴን አስመረጠኝ

ልፋለመው እንጂ ትግሥቱ ሰለቸኝ

እረጋ በል ቢሉኝ መቼ ሊገባኝ

ነፃነት አጥቼ መብት ሳይኖረኝ

ልቤም ተቸግራ ወጥሮ ይዞኝ

This document was created using Smart PDF Creator
To remove this message purchase the product at www.SmartPDFCreator.com

እምቢ ልበልና ወንድነት ይውጣኝ

ይፈንቅል ይታገል ይተርተርልኝ

ያበጠው ይፈንዳ ቀኑ ናፈቀኝ

በላይ እንዳልነበርሽ አገሬ ኩራቴ

መታፈሪያ ሆነሽ የእኔ ማንነቴ

በላይ እልሻለሁ እስከለተ ሞቴ

፩፩/፪፲/፩፩

This document was created using Smart PDF Creator
To remove this message purchase the product at www.SmartPDFCreator.com